## የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ህብረት ለምርጫ በድምፅ መስጫ ቀን ስለሚያደርገው ትዝብት የተሰጠ መግለጫ

**አርብ፤ ሰኔ 11፣ 2013 ዓ.ም**

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በበርካታ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ላይ የሚታየውን ረዣዥም ሰልፎች ተከትሎ የድምፅ መስጫ ሰዓቱን ማራዘሙን ያደንቃል። ይህም ዜጐች ድምፅ የመስጠት መብታቸውን በሚገባ እንዲገለገሉበት እድል የሚያሰፋ መሆኑ በጐ ውሳኔ ነው።

በአንፃሩ ህብረቱ የምርጫ ሂደት ጅማሬውን አስመልክቶ ቀደም ሲል በዚሁ እለት የሰጠውን መግለጫ ተከትሎ የምርጫ ትዝብቱን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፤ ከድምፅ መስጥርት ሂደቱ ጅማሬ አንስቶ በጠቅላላው 304 የአሳሳቢ ኩነት ሪፖርቶችን ተቀብሏል። ከእነዚህም ውስጥ 166 ያህል ሪፖርቶችን አጣርቶ አረጋግጧል።

ህብረቱ በዚህ አጭር መግለጫው 2 ዋና ዋና ነጥቦችን ማንሳት ይፈልጋል

1) **የምርጫ ጣቢያ ቁሳቆሶች እጥረት**

   በበርካታ አካባቢዎች በተለይም በጋምቤላ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ታዛቢዎቻችን ከተዘዋወሩባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በ56 የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ወረቀትን ጨምሮ ተያያዥ የድምፅ መስጫ ቁሳቁስ እጥረት ታይቷል፤

2) **የምርጫ አስፈፃሚዎች መዳደል**

   በአዲስ አበባ ከተማ እንዲሁም በሲዳማ እና በደቡብ ክልሎች በአጠቃላይ በ10 የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጠት ሂደቱን የሚመሩ የምርጫ አስፈፃሚዎች ብዛት በቦርዱ መመሪያ ላይ ከተጠቀሰው ዝቅተኛ ቁጥር ያነሰ ሲሆን፤ ይህም የድምፅ መስጠት ሂደቱን ከማጓተቱም ባሻገር በቀሪ የምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ የሚኖረው የስራ ጫና ለትኩረት ማጣት፣ ለስህተት እና ላልተፈለገ ተግባር እንዳያጋልጥ ያሰጋል፤

3) **ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በድምፅ ጣቢያ ውስጥ መገኘት**

   ታዛቢዎቻችን ከታዘቧቸው ጣቢያዎች መካከል በቦርዱ መመሪያ መሠረት በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንዲገኙ ከተፈቀደላቸው ውጪ በ10 የምርጫ ጣቢያዎች ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ተገኝተዋል።

ህብረቱ ታዛቢዎቹ የሚያደርሱትን የምርጫ ትዝብት መረጃዎች በተከታታይ እየተቀበለ ማጣራቱን እና ማረጋገጡን ይቀጥላል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድም ሆነ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል የአስተዳደር እና የፀጥታ አካላት የድምፅ መስጠት እና የቆጠራ ሂደቱ በተቻለ መጠን እንዲጠናቀቅ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ህብረቱ ጥሪውን ያስተላልፋል።